EthioLion

# ባንድ እራስ ሁለት ምላስ

ከሳሙኤል ሽፈራው ዳላስ

አቶ በቀለ ተክሌ አንድ መጣጥፍ ውስጥ ለውስጥ አስተላልፈው ነበር። በዚያ የግል እምነታቸውን ግልጽ አድርገዋል። የግል እምነትን መሸሽግ እንጅ በግልጽ ይህ ነው ብሎ ለዚያ መታገል ወይም መከራከር ተገቢ ነው። በበኩሌ በአንድ እራስ ሁለት ም ላስ እንዲሉ የልብን በልብ አርጎ ለፍጆታ ማለትም ሌላውን ሳያስቀይሙ የተቀረጠረ ጠ ባሕርይ ማሳየት ነው አስገማችም ፣ አስጠርጣሪም ይመስለኛል እና እምነታቸው ግልጽ ለማረግ በተለዋወጡት ደብዳቤ(email) ለትችት ብንሔድበት ለዚህ ጽሁፍ አ ቅራቢ ተገቢ መስሎ ስለታየ በሰለጠነ ውይይት ለመቀጠል ተስፋ በማድረግ ይህን የ ግል አስተያየቴን አቀርባለሁ ። ለዚህ ትችቴ መነሻ ምክንያት፤ በዚህ በዳላስ ለአለፉ ት ሦስት አመታት የቀጠለው የቤተክርስቲያናችን ችግር ዛሬ አልፎ ወደመላ ዜጋ በ መዳረሱ ፤ ችግራችንና ገመናችን ከኛ አልፎ ለአሜሪካውያንም በቴሌቪዥን መስኮት ስለደረሰ ። በአካልና በጽሁፍ ትችና አስተያየት ቢደረግ፤ የሁሉም ፍላጎትና እምነት ግልጽ ወጥቶ ይለይለታል ወይም ያስማማናል ከሚል እምነት ይህችን አጭር አስተያ የቴን አቅረብሁ። ይህን ያገኛችሁ ወገኖችም ልትነጋገሩበት፤ ልትተቹበትም ይገባል እላለሁ። በዚህ ጽሁፌ የምተቻቸው ግለሰብ በኤሌክትሮኒክስ ልውውጥ ከተገኘ ጽሁ ፋቸው በመመርኮዝ ነው። ለትችት ያበቃኝም ግለሰቡ የቤተክርስቲያንን ደንብ በቅ ጡ የሚያውቁና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የተንሰራፋውን የአንድ አንባ ገነን አባት ባደባባይ የሚያወግዙ በድብቅ ግን የሚደግፉ ሆኖ ስላገኘሁት። ብሎም እ ዚህ ዳላስ ችግሩ ከጊዜ ጊዜ እያመረቀዘ ምእመናንን ስላስቸገረ፤ ከግልጽ ልውውጥ ሊገኝ የሚችል ስምምነትና በአንድ እራስ ሁለት እምነት ከመግፋትና ወዳጅ ወገንን ከማደናገር ግልጽነትን ለመፍጠር በማሰብ ነው።

አቶ በቀለ ተክሌ በኢንተርኔት በደብዳቤ መልክ ያስተላለፏቸው ሁለት መጣጥፎች ይመስሉኛል አንዱ የግል የብእር ስም በመጠቀም ሲሆን ሌላው በትክክለኛ ስማቸው ነው። እኔም በሁለቱ መጣጥፎቻቸው ላይ ለመተቸት ስከፍል ከላይ ከታች አውርጀ ና አውጥቸ ተመልክቸ ሲሆን ለመዘግየቴ ዋናው ምክንያት አንድም ጽሁፉን ላወጣበ ት የሚያስችለኝ ድሕረገጽ ፍለጋ ሲሆን (ባካባቢ ማለት ነው)፤ ሌላው ተሰደብን የ ሚል ችግር እንዳያስከትል በመስጋት ነው።

EthioLion

በመጨረሻ የመላ ኢትዮጵያውያንን ሐይማኖታዊና ፖለቲካዊ እምነት ተመልካች ጽሁፍ በመሆኑ በኢትዮጵያውያን ድሕረገጾች ቢወጣ ጸሐፊውም ይፋ መልስ ይሰጡበታል አለያም በእምነታቸው ይከራከሩበታል በሚል ወደ ድሕረገጾች ወስጀዋለሁ።

የአቶ በቀለ ተክሌ ጽሁፍ እንዲህ ይጀምራል።

የቤተ-ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች ወይም መሪዎች መሆን የሚገባቸው ካህናት ናቸው። በዚህ ሀገር አመራሩን ምእመናን የሚቆጣጠሩት ፈቃድ አወጣጡ ከአገራችን ለየት ያለ በመሆኑና የኢትዮጵያ ቤተ-ክርስቲያን ግንባር ቀደም መስራች ወይም ሰብሳቢ ሆና በሷ ቁጥጥር ሥር ስላልተቋቋሙ ነው። ከተቋቋሙም በኋላ አመራሩ ወደ እሷ እንዲመለስ የምታደርገው ጥረት ስለሌለ ነው። ቤተ-ክርስቲያን ሲቋቋም የሚያቋቁመው ሰው ወይም ቡድን የኢትዮጵያን ቤተ-ክርስቲያን መሪዎችን አያስፈቅድም። የሚያስመጣው ካህን ጋር ነው ግንኙነቱ። ያ ካህን ደግሞ የሚከበርና የራሱ አለቃ የሚሆን ስለሚመስለው የሚመጣው ተደብቆ ነው።

ሲኖዶሱ በዚህ አኳኋር ያሉትን አያተ-ክርስቲያናት በአተዳደሩ ለማጠቃለል ሀፍረት የያዘው ይመስላል። ወይም ምእመናኑ እስከሚጠይቁት ድረስ ዝምተኛነቱን መርጧል ። ወይም በራሳቸው ፈቃድ የተቋቋሙ ስለሆኑ ከሥነ-ሥርዓት የወጡ፣ የማይበጁት (የማይታዘዙት) አመፀኞች ናቸው ብሎ ንቆ ትቷቸው ይሆናል። ወላጆቿን ሳታስፈቅድ በራሷ ሥልጣን ባል የምታገባ ልጅ ወላጆቿ ችላ እንደሚሏት። ወላጆችዋና ልጇቱ ሊታረቁ የሚችሉት እንዴት ነው? ወይስ እንደተኮራረፉ ይቀራሉ?

ጸሐፊው የሚያወሩት በውጭ ሐገራት የተቋቋሙ አቢያተክርስቲያናትን አስመልክቶ ሲሆን ቤተክርስቲያናቱ በውጭ ከተከፈቱ በኋላ ምእመናኑ በያሉበት አገር ሕግጋት ስር የአስተዳደር ጉዳይን ስላያያዙት መቀጠል የሌለባቸው መሆኑን ለአቡነ ጳውሎስ መራሹ ሲኖዶስ ያሳስባል። እንደጸሐፊው ለዚህ ያበቃን የሲኖዶስ ቸልተኝነት መሆኑን (ጳውሎስ መራሹን) በመቆጨት በምሳሌ ያቀረባት ያለወላጆቹአ ፈቃድ ባል ያገባች ልጅን ከወላጆቿ የተቆራረጠች መሆኗን እና ለመታረቅም መውሰድ ያለባትን የወላጆቿን ፈቃድ መከተልና የሚመርጡላትን መቀበል። አለያ ትዳሯን ከመረጠች ከቤተሰቧ ላትገናኝ መቁረጧን መቀበል ይላል።

እስኪ አቢይ የዚህን ትችት አላማ ወደሆነው ትኩረት ላርግና፣ እንደ ጸሐፊው አስተሳሰብ ከሆነ በውጭም ይሁን በውስጥ ያሉ አቢያተ ክርስቲያናትና ምእመናን የአቡነ ጳውሎስን ቅዱስ አባትነት ካልተቀበሉ መዘጋት ይኖርባቸዋል የሚል ፍርደ ገምድልነት ያለው አስተሳሰብ ይነግረናል። እኛ ያልነው ብቻ ትክክል የሚለው አስተሳሰብ ከ

EthioLion.com

መሪው ከፖለቲካ ሹመኛው ጳውሎስ ጀምሮ የተላበሱት በመሆኑ ባይገርመንም። በ ጭቆና ቀንበር ታፍነውና ተገደው ያለቤተ ክርስቲያኗ ሕግና ደንብ አባት ሳያልፍ በ ሕይወት እየኖረ መንበረ ስልጣኑን ከህግ ውጭ የጨበጡ የባለጊዜ ተሿሚን ያልተከ ተለ ሁሉ መወገዝ አለባቸው። ያልተቀበሉ ቀሳውስትም ቅስናቸውን መነጠቅ ይኖርባ ቸዋል ይለናል። ከሊቁ ደቀመዝሙሩ እንዲሉ፣ ጸሐፊው የጳውሎስን ቦታ ቢይዙ ከ ሳቸው የባሰ ለመሆናቸው ይህ ጽሁፋቸው ያሳያል።

የጸሐፊው ምሳሌ አቀራረብና በውጭ የአቡነ ጳውሎስን ፓትሪያርክነት ያልተቀበሉ ምእመናንም ሆነ አቢያተ ክርስቲያናትን አስመልክቶ የማይገናኝ ቢሆንም። ለመሆኑ በዚህ ጊዜና ዘመን ቤተሰብ በወደዱት ሰው እንድትዳር የሚያደርግ ባሕልን እንደመ ልካም ማቅረቡ እራሱን የቻለ ችግር ያለበት አስተሳሰብ መሆኑን ከጸሀፊው የኋልዮሽ ጉዞ መመልከት የሚቻል ይመስለኛል። በውጭ የተመሰረቱ አቢያተ ክርስቲያናትን አስመልክቶ በአቡነ ጳውሎስ መንበረ ስልጣን ስር ካልሆኑ እንደ ብልግና መቁጠሩን ና፤ ለብልግናቸው መነሻ ሐይ ማለት የሚገባቸው አባት (አቡነ ጳውሎስ ማለታቸው ነው) ቸልታ መሆኑን ያሳየናል። ለዚህ በአቡነ ጳውሎስ የሚመራው ሲኖዶስ ሐፍረ ት እንደያዘው ያሳይና በመቀጠል እንዲ ይላል።

“ስለሆነም፣ በቅድሚያ በዚህ በውጭ ሀገር ከሲኖዶሱ ቁጥጥር ውጭ ሆነው ያሉት ካህናት ደህናዎቹ (ኑፋቄ የሌለባቸው) በሲኖዶሱ አስተዳደር ሥር እንዲሆኑ እንዲጠ የቁ። ፈቃደኞች ያልሆኑትን ሥልጣነ-ክህነታቸውን መግፈፍ ይገባል”። ይላሉ ጸሐ ፊው።

ፕትርክናውን በባለጊዜወች ተሹመው የያዙት አባት እንኳን ይህን ለማድረግ አልከጀ ሉም። ምክንያታቸው ግልጽ ነው። ቢፈልጉም የማይችሉ በመሆናቸው ቀሳውስትን ሊገፉ፤ አቢያተክርስቲያናትን ሊዘጉ፣ የሚያስችል ስልጣን የላቸውም። ለዚያውስ የ ራሳቸው ስልጣን ከገዥወች ባለፈ ሕጋዊነቱ በሕዝብ ባለመሆኑ፤ በየሄዱበት ከእንቁላ ል ዱላው እንኳን አላተረፉቸውም።

ምንም እንኳን ጽሁፉ በያዘው እርእስ ላይ ማተኮሩን ቢተውም በተዛማጅ በውጭ አ ገራት በስደት ስለመጡ ቄሳውስት ጉዳይ የግል መብታቸውን የሚጋፉ አስተያየት በ መግባት፣ በአቡነ ጳውሎስ ስር ያልሆኑ፣ አባትነታቸውን ያልተቀበሉ፣ ከሳቸው ው ጭ በየቤተክርስቲያኑ ለሚያገለግሉ ሁሉ ተጠይቀው አይሆንም ያሉት ቅስናቸው ይገ ፈፍ ይሉናል። ጸሐፊው ከሁሉም በላይ የሳቱት ነገር ለመሆኑ በስደት ላይ ያሉት አ ባቶችን ለስደት የዳረገቸው ዋና ጉዳይ ምን ይሆን ብለው አስበው ነውና በጳውሎስ ስር ካልሆኑ ቅስና የላቸውም የሚሉን? ባለፈው አመት እንዳስተዋልነው፣ እንደሰማነ

EthioLion

ው ልበል የሲኖዶስ አባቶች አቦይ ጸሐየ የተባለው የወያኔ ሹም  ከአንድ ሌላ የመን
ግስት ተወካይ ጋር በመሆን የቅዱስ ሲኖዶሱን ስብሰባ ተካፍለው ነበር። በዚያም ስ
ብሰባ የጳውሎስን የግፍ አመራር የተቃወሙ አባቶች ግልጽ የሆነ ቅሬታቸውን ለነዚ
ሁ የወያኔ መንግስት አባላት አሰምተዋል። ያንን ስብሰባ እንዳጠናቀቁ የጠበቃቸው በ
መኖሪያ ቤታችው የወያኔ/ኢሕአዴግ ፖሊሶች ጨለማ ለብሰው በተቃዋሚ የሲኖዶስ
አባቶች ላይ ድብደባና ጉዳት አድርሰውባቸው እንደነበር በአሜሪካን ድምጽ ሬዲዮ
በዜናና በቃለመጠይቅ አዳምጠናል። አቶ በቀለ ተክሌ ይህን ጭቆና በመቃወም በው
ጭ ለመኖር የተገደዱትን አባቶች ጨምሮ ክሕነታቸው ይነጠቅ ይሉናል። ማንም ሰ
ው ያለውን ስርአትም መደገፍ ሆነ ተሿሚውን ሕገወጥ ፓትርያርክ መቀበል መብቱ
ሆኖ ሳለ የሌሎችን መብት ለመገደብ መነሳትን ምን አመጣው? አገር ውስጥ ያሉ የ
ግፍ ቀንበር የተጫነባቸው ዜጎችም ሆኑ የሐይማኖት አባቶች ምርጫቸው አንድ ነው
። ሌላ ሊመርጡም ሆነ ሊያስቡ አይፈቀድላቸውም። ታች አምና እንዳየነው የሲኖዶ
ስ አባላት የሆኑ አባቶችን ሳይቀር ለድብደባ ያበቃቸው ስርአት ተጓደለ በማለታቸው
ነበር። ባገራችን እምነትን ጨምሮ በነጻነት ለማምለክ እጅግ የከበደ ሁናቴ ነው ያለ
ው። ያንን መሰል ስርአት ወደ ነጻው አለም ስደተኛ ለማምጣት መከጀል ከቅዠት ያ
ለፈ ሕመም ብንለው ስድብ ካልተባለብን መልካም ፍች ይመስለኛል። በአቶ በቀለ
ተክሌ እምነት ሕገወጡ ፓትርያርክ ይሁን ያላሉት ቤተ ክርስቲያንም ሆነ በሳቸው
ስር የማይተዳደር ቄስ መኖር የለበትም ባይ ነው። እውነተኛው ግን በውጭ በስደት
የሚኖሩ አባቶችን ሕገወጥ የሆነ ፓትርያርክ ስልጣናቸውን ሊነጥቅ አይችልም መብ
ቱም አይደለም። አቡነ ይስሐቅ እንዳልተቀበሉት ሁሉ ማንም አባት ሕጋዊነት የጎደ
ላቸውን ፓትርያርክ ያለመቀበል የሀይማኖት ግዴታው ጭምር ነው። ጸሐፊ እረስቶ
ት ካልሆነ ባገር ውስጥ እንዴውም ማህል አዲስ አበባ የልደታ ምእመናንና ቀሳውስ
ት በፖሊስ ሐይል እስከተገደዱበት ቀን ለአመታት የሕገወጡን ፓትርያርክ አባትነት
ሳይቀበሉ መቆየታቸው ይታወሳል። ዛሬም ድረስ በመላ አገሪቱ ያሉ አድባራትና ቀሳ
ውስት ተቀብለዋል ለማለት የሚያስችል ሰነድ የለም። በቤተክርስቲያኗ አንቱ ተብለ
ው የኖሩት ሊቀ ሊቃውንት አለቃ አያሌው ታምሩ እስከ እለተ ህልፈታቸው የኒሁን
ፓትርያርክ አባትነት ሳይቀበሉ በኑዛዜአቸውም የሐይማኖታችንን ስርአት ባጎደለ አባ
ት እሬሳየ አይባረክ በማለታቸው ያለስርአተ ፍታት ስርአተ ቀብራቸው ተከናውኗል
። “ጌታዋን የተማመነች በግ ላቷን ውጭ ታሳድራለች” እንደሚባለው ማለት ነው።
አቶ በቀለ ተክሌ ኦርቶዶክሳዊ ሐይማኖታችንን ለመንጠቅ ወሰነ። አቡነ ጳውሎስን
ልተቀበለ ሁሉ ኦርቶዶክስ አይደሉም አለን። ባስቸኳይ አዋጅ እንዲደረግና በውጭ
ያሉ አብያተ ክርስቲያናት የሚያገለግሉ ሁሉ ቅስናቸው ይገፈፍ ዘንድ ጠየቀ።

የዳላስ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያንን ለማፈረስ እየተካሄደ ያልው ሴራ ዘረፈ ብዙ
ነው። በአደባባይ አቶ በቀለና መሰል ግለሰቦች፤ በአባላት ተመርጠው የሚያስተዳድ

EthioLion.com

EthioLion

ሩ የቦርድ አባላትን ይኮንናሉ። ስራቸውን ያወግዛሉ። ችግር ብለው የሚያቀርቡት መ ብታችን ተጓደለ በሚል ሲሆን በውስጥ ለውስጥና በድብቅ ስብሰባወች ወይም በኢሜ ል ልውውጦች ይህን ያክል አጉራ ዘለል የሆነ ከኛ በቀር ኦርቶዶክስ የለም። አቡነ ጳውሎስን የማይቀበል ምእመን ሁሉ ኦርቶዶክሳዊ አይደለም። ቀሳውስቱም ቅስናቸ ው መገፈፍ ይገባዋል ይላሉ። ዞሮ ዞሮ አላማና ተግባራቸው ቤተክርስቲያኗን ለማፍ ረስ። ከነሱ ቁጥጥር ውጭ የሆነውን ስደተኛ ዜጋ በሐይማኖታዊ ቤቱ ተገናኝቶ፣ ጸ ሎት አድርሶ እንዳይለያይ ያዋክቡታል። በዳላስ ቅዱስ ሚካኤል ያላቋረጠ ክስ በታ ወቁ የስርአቱ ደጋፊወች ፋይናንስ አድራጊነት ቀጥሏል። ይህን የስደተኛ ምእመናን ቤት ለማፍረስ መብታችን ተደፈረ በሚል ሰበብ ወከባውን ቀጥለዋል። እውሸት ሲደ ጋገም፣ እውነት ይሆናል በሚል ፈሊጥ። የመብት ጥያቄን በክስ አጅለው ማህበረሰቡ ንና ምእመናንን ለማሳመን በየ ጓዳው ሁሉ ገብተው እያናከሱን ነው። በአገራችን ም ርጫ ተካሄደ በተባለበትና ወያኔ 99% ወንበር አገኘሁ ባለበት ወቅት፤ የዳላስ ኢትዮ ጵያውያን በተሌቪዥን በወጣ የሐሰት ዜና ልባቸው ተወስዶ። በስደት አገራቸው የሌ ለባቸውን ገመና ተቀብለው የሚምሰለሰሉበት ወቅት በመሆኑ። በአገር ስለተከናወነው ሽፍጥ የሚያውቁት አንድም ነገር አልነበረም።

አቶ በቀለ ተክሌ በዚሁ የዳላስ ኦርቶዶክስ አማኒያንን አልፎ ጠቅላላ ስደተኛ ዜጋው ን አንገት ያስደፋውን ይህን በሐይማኖት ሳቢያ የተዘየደ ሴራ ከመቀላቀል በፊት፤ ለ ሐይማኖት ተቆርቋሪ በመሆን በውነትም የብዙ ዎገኖችን እምነት ያተረፉ ወንድም ሆኖው እያለ በአደባባይ የተላበሱትን ጨዋነት፣ መከበር፣ ከግምት ሳያስገቡ በዘር ተ ዋቅሮ፣ በዘር በተመሰረተ ቤተክርስቲያን አባል ከመሆን በላይ። መሆን መብት ሆኖ እያለ፤ የኖሩበትን ቤተክርስቲያን ለምን በጳውሎስ ስር አልተዳደረም በሚል የውስጥ ብስጭት፤ በአደባባይ የምእመናን መብት ተገፈፈ በሚል የሐሰት ክስ አራሳቸውን ጨምሮ ከመሰሎች ጋር ላለፉት ሁለት አመታት ፍርድ ቤት ቤተክርስቲያንን በማቆ ም፤ ሌላ ጊዜ አጉል ግርግር በመፍጠርና የሌለብንን ገመና በተደለለ ሪፖርተር አው ጥቶ በቴሌቪዥን (primetime news) በማድረግ ኢትዮጵያውያን በተከበርንበትና በለፍቶ አደርነት፣ ጨዋነት በምንታወቅበት አዲስ ስም ካሰጡን ክፍሎች ጋር ወግነ ው መክረውና አብረው፣ በጎን የሌላ ቤተክርስቲያን አባል በመሆን። የንጹ ዜጎችና ምእመናን የጸሎት ቤት የሆነውን ቅዱስ ሚካኤል ቢቻል በጃቸው አስገብተው ለጳው ሎስ ካልተቻለ እረፍት አሳጥተው፣ ከሰውና አዋክበው እንዲዘጋ ለማረግ ባላቋረጠ ጭቅጭቅ ካስገቡን ወገኖች አንዱ ናቸው ብል፤ የሀሰት ክስ ሳይሆን፤ መልስ የሚፈ ልግ ጊዜ ሲያልፍም የሚያስተዛዝብ ጉዳይ ይመስለኛል።

የመላ ምእመናን የጋራ የሐይማኖት ቤት የሆነውን ለማዳከም፣ ብሎም ለማዘጋት ሲነ ሳሱ፡ አቶ በቀለና መሰል አባሪ ተባባሪወች። የነሱን ጥግ ይዘው በአንድ ቁስ በዘር

ተመርኩዞ በግል በመሰረተው ቤተክርስቲያን እራሳቸውን ጥግ ሰጠው ለመሆኑ ማን ም የዳላስ ዜጋ የሚያውቀው ጉዳይ ነው። እነዚህ የአባ ጳውሎስንም ሆነ ይህ አሁን የተጠጉበትን በዘር ተመርኩዞ ሕዝበክርስቲያንን ያንጓለለ ክፍል እንደ ትክክለኛ ደን ብ አክባሪ ቆጥሮ፤ ተገፍተው ካገር ተባረው በስደት የሚኖሩ አባቶችንም ሆነ ቀሳው ስትን ክብረ ነክ በሆነ ተሰምቶ፣ ታይቶ በማይታወቅ ቅስናቸውን ግፈፉ ብሎ ትዛዝ፤ እብሪትነቱን ብንዘለው፡ የጠያቂውን ማንነትና ምንነት ብንጠይቅ ደፈራችሁ አያሰኝ ም። የሚገርመው ትናንት በሰርቶ አደር ፓርቲ የካድሬ ያክል ተሿሚ የነበሩ ዛሬ ከ ጳጳሳት በዘለለ የሐይማኖቱ አራጊ ፈጣሪ ለመሆን ሲከጅሉ ሳይ ይህ ሁለት ተለዋዋ ጭ የሰውነት ባሕርያቸው ያስገርመኛል።

ሰሞኑንም እንዳየነው እርቅ ብሎ የጠራው የአቡነ ጳውሎስ አመራር ከሌሎች አባቶች ጋር ያሰበው የእርቅ አይነት ያው እነደፖለቲከኛ ወገኖቻቸው 99% እነሱ የበላይነቱን እስከያዙ ብቻ ለመሆኑ በተሰጠው መግለጫ ለማይት ችለናል። አባ ጳውሎስ ድፍረታቸው ከሐይማኖታችን ጋር በጣሙን የሚጋጭ በመሆኑም፤ በቁም እያሉ ሀውልት እንዲቆምለቸው በሰጡት ትእዛዝ ከነ ሰማእታቱ አቡነ ጴጥሮስ፣ አቡነ ሚካኤልና፣ አቡነ ቴወፍሎስ ጋር እርሳቸውን አስቀምጠዋል። ልብ ያስባል ይባል አይደል። ለዚህ ትችት ያነሳሳኝ የጠቀስኳቸው ግለሰብ ያው ሐውልት እንዳቆሙት ሁሉ እሳቸውን ያልተቀበለ ቤተክርስቲያንም ሆነ ምእመን ኦርቶዶክስ አይደለም ስሙን ይቀይር። ቀሳውስቱም ቅስናቸውን ይገፈፉ በማለታቸው ነው። የኔ መልእክት ለኒሁ በግብዝነት ወይስ በእብሪት ልበለው ለሰጡት ሐሳብ አዙረው ተመልክተው እርማት እንዲያደርጉ። በተጨማሪም አሁን እሳቸው ወደአንድ በዘር ተመስርቶ በተቋቋመ ጋር በመሆናቸው የቅዱስ ሚካኤልን ጉዳይ ለአባላቱ መተው። ማንኛውም እስካሁን የቀጠለው ክስና የቅዱስ ሚካኤል ምእመናንን እረፍት ከሚነሳ ነገር መቆጠብ። የሰሩትን ሁሉ አይተውና ተገንዝበው ወደ እውነታው መመለስ። የሌሎችን ምርጫ ማክበርና መቀበልም ቢችሉ መልካም ነው። እንደ አቶ በቀለ ባደባባይ ጳውሎስን እቃወማለሁ እያሉ በውስጥ ለውስጥ የጳውሎስን ስም ያልጠራ ሁሉ ጠላቴ ብለው እስከ ፍርድ ቤት እየጎተቱን ያሉ ወገኖች፤ መልካሙን አይተው የግል እምነት ክቡር ነውና የነሱን እንደምናከብር ሁሉ የኛንም አክብረው፤ የክበር ተከባበር መንፈስ ብንፈጥር ለጤናችንም፣ ለመልካም ግንኙነታችንም በጎ ነው እያልሁ እሰናበታለሁ።